መሠረታዊ መብቱ ሲከበር ብቻ ነው፡፡ እለበለዚያ በኩሉኔልና በሻለቃ መሃል፡ በኢሠፓ ፋሽስታዊው መንጋ መሃል ምርጫ ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ ከመሆን አያልፍም፡፡ የመደራጀትና የመቃወምን መብት ገድቦና ከልክሎ ዴሞክራሲ ሰፍኗል ብሎ መመጻደቅ በፋሽስቱ መንግሥት የተጀመረ ባይሆንም በዚህ መንግሥት እንደመለያ ፖሊሲ የተወሰደ ተራ ማጭበርበሪያና ባዶ መሸንገሊያ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ በኢሠፓ አይወከልም - ይህንን ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ሃቀኛ ወኪሎችን በነፃ ለመምረጥና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት ሕዝቡ ይሻል - ይህ የማይካድ ነው፡፡

ለዚህ ትግል ተባብሮ መሰለፍ ሀገራዊና ዴሞክራሲያዊ ግዴታ ነው፡፡

ሃቀኛ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በሕዝባዊ ትግል ድል

ትመሠረታለች! !

የሕዝቡ በፖለቲካ ድርጅት የመደራጀት መብት በሕዝባዊ

ድል ይረጋገጣል!!

እ ና ቸ ን ፋ ለ ን! ! !

---

በሚያዝያ 1978 ዓ.ም. ኢሕአፓ 14 ዓመት

በሚያዝያ 1978 ዓ.ም. ኢሕአፓ የተመሠረተበትን ዓሥራ አራተኛ ዓመት ያከብራል፡፡ በጀግና አባሎቹ የመስዋዕትነት ደም የቀላውን "የትግል ሰንደቁን" እያውለበለበ የቀጠለው ኢሕአፓ በዚህ ወቅት ለሕዝብ የገባውን ቃል-ኪዳን ያድሳል፡ ትግሉን ያፋፍማል፡፡

---

የ ጎሠፌዩ